# የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ

ለንደን
ሚያዝያ 1994

# የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የረጂም ጊዜ ታሪክ ዉስጥ ፈታኝና በታኝ ሁንታዎች በተለያዩ ዘመናት ተከሰተዋል። በዘ
መኑ የነበረዉም ትዉልድ ባለዉ አቅምና እዉቀት እየሰራና እየተሰዋ *ሀገሪቱን እስካለንበት ጊዜ* አ
ቆይቶ ላሁኑ ትዉልድ አስረክቦአል።

ይሁን እንጂ ሀገሪቱዋን ከገጠሙዋት ፈተናወች መካከል አንዳንዶቹ ጊዜና ወቅት ጠብቀዉ በዉስጥ
ከሃዲዎች አማካይነት ስለሚፈጸሙ፤ ትግሉን አስቸጋሪና ዉስብስብ ሲያደርገዉ ቆይቶአል።

ያሁኑም የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ካለፉት ዘመናት ጋር የተያያዘና ህዝቡን በመለያየት በማያቋርጥ
ብጥብጥ ዉሰጥ ከቶ ህዝቡዋ እርስበርሱ በሚያደርገዉ መተናነቅ እንዲዳከምና ህልዉናዉን እንዲያ
ጣ ለማድረግ ነዉ። በጣም የሚያሳዝነዉና የሚያሳፍረዉ ይህ ጥፋት የሚፈጸመዉ በዲሞክራሲ፣ በእ
ኩልነትና በብሄረሰቦች ስም መሆኑ ነዉ።

የብሄር ብሄረሰብ ጉዳይም ትልቁ ማስመሰያና መነገጃ ሆነ። ለረጂም ዘመናት እንደባህል ሆኖ የቆየዉ
የኢትዮጵያዉያን በተለያዩ መንግስታት ዘመን በጋራ ላንድ ሀገር ህዝብ ጥቅም የመታገል ባህል እንዲ
ከስምና ህዞቦች ተነጣጠለዉ ወደ እድገት ሳሆን የጎሪጥ በመተያየት ከሰላምና ከእድገት ጎዳና እንዲ
ዎጡ ብሎም በጠላት በቀላሉ እንዲጠቁ ተቀይሶአል።

ይህንን እኩይ አመለካከታቸዉን ሲያቀርቡና ሲከራከሩ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ የጠለቀ እዉቀት እንዳ
ላቸዉና ለሀገሪቱ ብሄር-ብሄረሰቦች እንደሚያዝኑ ሆነዉ ያዞ እንባ ያፈሳሉ። የሚቃወሟቸዉም ለራሳ
ቸዉ ጥቅም ሲሉ ብቻ እንደሆነ አድረገዉ ለማስርዳትም ሞክረዋል። ሀቁ ግን የአንድ ሀገር ህዝብ
ደህንነትና አንድነት ስገለሰብ ወይም ለአንድ ብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን በአጠቀላይ በሀገሪቱዋ ዉስጥ ለ
ሚኖሩ ዜጎች ሁሉ መሆኑን አሁን በአይናችን ያየነዉ ከኤርትራ ጋር የተደረገዉ ጦርነት ባስተማራቸ
ዉ ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዎገኖቹ የሚጠቅሙትን መፈክሮች ከማንሳትና ከነበሩት መሪዎቹ ጋር ለህዝብ ለ
ሚጠቅሙ ለዉጦች ከመታገል ወደኋላ ያለበት አንድም ጊዜ አልነበረም። ለምሳሌም ያህል የመሬት
ላራሹንና የዲሞክራሲን ጥያቄ አንስቶ በተለያየ ጊዜ መስዋእትነት ከፍሎአል። የብሀረሰቦችንም ሁለ
ንተናዊ ማንነት በአጠቃላይ የህዘባችንን ጥቅም ደህንነትና አንድነት አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ ለ
መተግበር ወደሁዋላ ያለበት ጊዜ አልነበረም።

ዛሬም ከበታኞችና ከዘረኞች ጋር በሀገርም ዉስጥም ሆነ በዉጭ የምንታገለዉ በአንድነት ላይ የተመ
ሰረተ የሰላም የእኩልነትና የእድገት ጎዳና እንዲቀየስ ነዉ እንጂ ወያኔ ለማደናገር እንደሚያሶሪዉ
የብሄር ብሄረሰቦችን መብተና ማንነት ለመጋፋት አይደለም። ወያኔ በብሄር ብሄረሰቦች ስም በኢትዮ
ጵያ ህዘብ ላይ የፈጸመዉን ግፍና ወንጀል ምንም ያህል ለማስመሰልና ለማደናገር ይሞክር እንጂ የ
ኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የአለም ሰላም ወዳድ ህብረተሰብም ጭምር በሚገባ ተረድቶታል።

ስለዚህ ታሪካችንንና ማንነታችንን በወያኔ ፕሮፓጋንዳ ሳናናጋ ጸንተን በመቆም ወደፊት ከጊዜ ጋር ህዝ
ባችን የሚያነሳቸዉንና የሚጠቅሙትን ነገሮች ማጤንና እዲፈጸሙ አስተዋጽኦ ማድረግ እንደ ወያኔ
አይነት ጸረ-ህዝብ ድረጂቶች በራሳችን ጥቃትን ስህተቶች በመጠቀም ህዝባችንን ሁከት ዉስጥ እንዳ
ያስገቡት ከመከላከሉም በላይ የሚፈሩት አንድነታችን እንዲጠናከር ያደርገዋል።

# ኢትዮጵያ ከደርግ ወዲህ

የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ለማየት ወያኔ አዲስ አበባ እዴት እንደገባና ከሻእቢያና ከለሎች ኢትዮጵያን ከሚቃረኑ ሀይሎች ጋር በመሆን በሰላም በዲሞክራሲና በብሄር-ብሄረሰቦች ስም የፈጸመዉንግፍና የተከተለዉን የጥፋት ጎዳና መቃኘት ያስፈልጋል።

ወያኔ የቀዝቃዛዉ ጦርነት ማለቅንና ኢትዮጵያ ዉስጥ የሰፈነዉን ሃላፊነት የጎደለዉ ወታደራዊ አምባገን የህዝብ ደጋፍ ማጣት ተጠቅሞ ስልጣን ከያዘ በኋላ ጸረ-ኢትዮጵያ ባህርዩን በሚከተሉት ተግባሮቹ ይፋ አደረጋቸዉ።

- ህዝብን በመከፋፈል ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በመሆን ኢትዮጵያን መስራች በሆነዉ የመላዉ አማራ ህብ ላይ አሳፋሪና ታሪክ ይቅር የማይለዉ ዘመቻ ተካሄደ። ለራሳቸዉ የጥፋት አላማ በሸንሽኑአቸዉ በኦሮሞ በደቡብ ባፋር በሱማሌና በመጨረሻም በራሱ በትግራይ ህዘብ ላይ የጥፋት ዘመቻዎቻቸዉን አሰፋ። ለምሳሌ ያህል የጅምላ ጭፍጨፋ የተካሄደባቸዉን የአረባጉጉን የበደኖን የአረሲን የጎንደሩን ያደባባይ ኢየሱስን የጌዲኦን የጉጂን ዎላይታ ሶዶን አረካን ምስራቅ ወለጋንና አዲስ አበባን ላብነት ማስታዎሱ በቂ ነዉ።

- ታሪኩንና ማንነቱን የማያዉቅ ሰዉ እራሱን የማያከብር ግራ የተጋባና በቀላሉ ወደ መሩት የጥፋት ጎዳና ሊጓዝ እንደሚችል በማመን የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ እንደሌለዉና ቢኖረዉም ከመቶ አመት እንደማይበልጥ በድፍረት በይፋ ተለፈፈ።

- ለኢትዮጵያና ለህዘቡዋ ያደሉና የተቆረቆሩ እንደነ ፕሮፌሰር አስራት ወ/የስ የመሳሰሉ ተገደሉ ታሰሩ የተረፉትም ተሰደዱ።

- ኢትዮጵያዊዉን የአማርኛ ፊደል ሳይቀር [1]ሳባ እያሉ መጥራት ጀመሩ.

- ታሪክን እያጣመሙ አርበኛዉን ከሀዲ፣ ከሃዲዉን አርበኛ አድርገዉ አቀረቡ። ሌሎች ለፍትህና ለነጻነታቸዉ የታገሉና የሚታገሉ ህዝቦች ሳይቀሩ የሚያከብሩዋትንና የሚኮሩባትን የኢትዮጵያን ሰንዳቅ አላማ ክብር በመንካት ባደባባይ ጥላቻቸዉን ገለጹ።

- ከወሎና ከጎንደር ሰፊ የሆነ ለም መሬት በመቁረጥ ወደትግራይ ቀላቀሉ።የተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎችና የመንግሰት ዜና ማሰራጫዎች ሳያቀሩ ታይቶ በማይታዎቅ ሁኔታ አንድን ብሄረሰብ በመነጠል ማገልገል የእለት ከእለት ስራቸዉ ሆነ።

- የኢትዮጵያ አካል የነበረችዉ የኤርትራ ክፍለ-ሀገር ያለምንም ቅደመ ሁኔታ በሁለቱም አካባቢ የሚኖሩ ወንድማማች ህዘቦች ረግተዉ ሳያሰቡበትና ሳይመካከሩበት በሀገወጥና ስርአት በሌለዉ መንገድ ድንበሩን እንኳን ህዝብ ሳያዉቀዉ እንዲለያዩ ከተደረገ በሁዋላ በዚሁ መዘዝ በተቀሰቀሰዉ ጦርነት ከፍተኛ የሰዉ ህይወትና ንብረት እንዲወድም ተደረገ።

- በህዝብ የተመረጠ ህጋዊ የኢትጵዮያ መንግስት መስሎ ለመታየትም የተጭበረበረ ምርጫ ተካሄደ።

- ነባር የሆነዉ የኢትዮጵያ ጦር በየትም ሀገር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እንደ ባእድ ጦር ተበተነ።ተሰደደ።

- የወያኔ በደል ያንገሸገሻቸዉ ተማሪዎችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለሰላማዊ ሰልፍ እንደወጡ ተጨፈጨፉ። የተረፉትም እንዲሰቃዩ በእስራት እንዲማቀቁና እንዲሰደዱ ተደረገ።

---

1

ንግስተ-ሳባ በመጽሃፍ ቅዱስ ሳይቅር የኢትዮጵያ ንግስት መሆኑዋ ቢታዎቅም በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ የመንን ጭምር ታስተዳድር ስለነበር የመኖችም የኛናት ዪላሉ። የአማርኛና የሳባ ፊደላት ግን የተለያዩ ናቸዉ።

## ኢትዮጵያና የኤርትራ ችግር

ወያኔ ስልጣን ከመያዙ በፊትም ሆነ ወዲያዉ እንደያዘ አካባቢ የጦርነት ምክንያቶችን ጠንቅቆ ባለ መረዳትና በተለይም የኢትዮጵያን ህዝብና መንግታት የኤርትራን ጦርነት ሆነ ብለዉ እንደፈጠሩት በ ማስመሰል ያልተናገረዉ ቃልና ያላቀረበዉ ጽሁፍ አልነበረም።

በአጼ ዮሃንስና በራስ አሉላ ዘመን ጀምሮ የነበረዉን የኤርትራን ችግር አጼ ምኒልክና ሌሎች ከዚያ ወዲህ የነበሩ የኢትዮጵያ መሪወች እንደፈጠሩት አድርገዉ አቀረቡት።

እአአ በስኔ 1983 ኤርትራን በሪፈረንደም ስም ወያኔ ሲያስገነጥል ዉሳኔዉ ህዘቦች ሳያዉቁትና ሳይመ ክሩበት ከመፈጸሙም በላይ የኢትዮጵያን ህዝብ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ምንም ሃሳብ እንዳይሰጥና እንዳ ይሳተፍ በሀይል በማፈን ስለተፈጸመ ቸግሩን የበለጠ አወሳሰቦ ወደፊትም እልባት እንዳያገኝ አድርጎ ት አልፎአል።

ይህ የኢትዮጵያን ህዝብ በመጋፋትና በጥናት ላይ ሳይሆን በጥላቻ ላይ የተመሰረተ የመገንጠልና የማ ስገንጠል ዉሳኔ ሊላዉ ቀርቶ የሚገነጠለዉ አካል ከየት ተነስቶ እስከየት ድረስ እንደሆነ እንኳን በግ ልጽ ያሳወቀ ወይም (define ያደረገ) አልነበረም።

እንዳወሩትም ጦርነትን ለማቆምና ሰላም ለማምጣት ሳይሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ታይቶ በማይ ታወቅ ሁኔታ በሁለት አመት ዉስጥ ብቻ በመቶ ሺ የሚቆጠር ህዝብ እንዲሞት እነዲቆስልና እንዲ ሰደድ ተደርጎአል። ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ከዚያች ድሀ ሀገር ህዝብ እየተወሰደ ለጦርነት ብቻ ሳይሆን ለግለሰቦች መክበሪያና መንደላቀቂያም ዉሏል።

ከዚያም ባሻገር ካንድ ሺህ ኪሎሜር በላይ የባህር በር ያለምንም ድርድር ካስረከቡ በሁዋላ በልዋእ ላይነት ስም በሰሜን ምእራብ ያን ያህል የከረረ ዉጊያ እንዲካሄድ መደረጉ ብዙወችን ግራ ያጋባና ያስደነቀ ጉዳይ ሲሆን በዉጭ ሀገርም 'The senseless war'
(ትርጉመቢሱ ጦረነት) በመባል ታዉቋል።

## ያልጀርሱ ስምምነት

ይህ ስምምነት ችገሩን ለመፍታት ሳይሆን ያወሳሰቡትን ችግር የበለጠ አዙሪት (vicious circle) ዉስጥ አስገብቶታል። የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ተገዥነት ጥያቄ ነዉ በማለት ተቀብሎ የማስገንጠሉን ስራ ካስተናገደ በሁዋላ ክፍለ ሀገሪቱዋ የምትገነጠል ከሆነ የመጨረሻዋ ቅኝ ገዥ (ኢትዮጵያ) ታስተ ዳድራት በነበረበት ጊዜ የነበራትን ድንበር ይዛ መለየት ይገባት ነበር። ከዚያም በላይ አሰብና አብዛኛ ዉ የቀይ ባህር ጠረፍ የሚገኘዉ መሬት ባፋር ራስ ገዝ ዉስጥ መሆኑ እየታወቀና የአፋርም ህዝብ በ ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ የቆየና አሁንም ከወንደሞቹ ላለመለየት የሚያደረገዉን ያላሰለሰ ትግል ማንሳት ቀርቶ ከግምት ዉስጥ ሳያስገቡ ኢትጵዮያ ይዞታዋን እንድታጣ ለማድረግ ሲባል ብቻ ቅኝ ገዢ ፍለጋ ወደ 1900 1902ና 1908 ሄደዋል።

የአልጀርሱ በኢትየጵያና በኤርትራ መካከል በወያኔ የተፈረመዉ ስምምነት አርቲክል አራት ቁጥር ሁለት እንዲህ ይላል 'The parties agree that a neutral boundary commission composed of five members shall be established with <u>the mandate to delimit and demarcate the colonial treaty border based on pertinent colonial treaties (1900, 1902 and 1908) and *applicable International low.*</u>

ወያኔ ሁልጊዜ በህጋዊነት ሽፋን የኢትጵያን ህዝብ ማዋረድ ትልቁ ተልእኮዉ መሆኑን ደጋግሞ አስመ ስክሯል። ከነዚህም ዉስጥ ታሪክ ሲያስታዉሰዉ የሚኖረዉና በጣም የሚያሳዝነዉ የኢትዮያ ድንበር የሚያሰነዉ የኤርትራ ቅኝ ገዥና በኢትዮጵያ ሰላማዊ ህዝብ ላይ በተደጋጋሚ በጠላትነት በመዝመት ሰላማዊ ህዝባችንን በጨፈጨፈችዉ የፋሽስቱዋ ኢጣሊያን ፈለግ በመከተል መሆኑ ነዉ።

ኢጣሊያ የኢትዮጵያ አካል ነበረዉን ህዝብ በመነጠልና ኤርትራ የሚባል ባአድ ስም እአአ በ1890 በመስጠት የረቀቀ የስነ ልቦና ጦርነት (Brainwashing)
አካሂዳለች። ባለማቋረጥ በተደረገዉ የፕሮፓጋንዳና አስተሳሰብን የመለወጥ ዘመቻ የኤርትራ ህዝብ የራሱን ወንድሞች እንዲጠላና በማያቋርጥ ጦርነት ዉስጥ እነዲዘፈቅ አድርጋለች።

በመላዉ አለም ፋሽቶቸና ናዚዎች እየታደኑ ለፍርድ በሚቀረቡበት በዚህ የአለም አቀፍ ሰባዊ መብት በጎለበተበት ባሁኑ ሰአት ወያኔ ሃገራችንን ብቻ ሳይሆን ለነጻነት የደከሙትን ህዝቦች ሁሉ ክብር በመንካት የምስማማዉ የጣሊያን ቅኝ ገዚዎች በከለሉት ድንበር ብቻ ነዉ በማለት ቅኝ ገዥነት ለተወሰኑ የሰዉ ዘሮች ብቻ የሚገባ ወይም የተሰጠ ጸጋ አድረጎ በመቀበል እራሱን ዝቅ አድርጓል።

ኢጣሊያ በተለያየ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ በጠላትነት ዘምታ ብዙ ህይወትና ንብረት አዉድማለች። በተለይም በ1935-1941 (በሁለተኛዉ ያለም ጦረነት) በአለም አቀፍ በተወገዘ የመርዝ ጭስ (Chemical/ BiologicalWeapon) የኢትዮጵያን ሰላማዊ ህዝብና እንስሳት ጭምር ያለአርህራሄ ጨፍጭፋለች።

አቶ ዮሃንስ መሸሻ storiaillustrata)የሚባለዉንመጽሀፍ በመጥቀስ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የካቲት 12 ቀን 1929 አዲስ አበባ ዉስጥ ፋሽስቶችና ቅጥረኞቻቸዉ (ባንዶቻቸዉ) ያደረጉትን የሚዘገንን ጭፍጨፋ እንዲህ ሲሉ ገልጸዉታል «ህዝቡን እቤት ዉስጥ እንዳለ እሳት ለቀቁበት እዉጭ የተገኘዉን በጥይትና በመትረየስ ደፉት፣ በሰደፍ ጭንቅላቱን ፈተፈጠዉ እየተንቀጠቀጠ ሲሞት የገደለዉ ፋሺስት በእግሩ ረግጦ ፎቶገራፍ ይነሳል፣ በድልድይ አጠገብ የተያዙትን ገፍትረዉ በመጣል ሲወድቁ ከላ ይሆነዉ በጥይት ጨፈጨፉአቸዉ፣ ሴቶችም ሆኑ ህጻናት እድሜና ጾታ አላዳናቸዉም።»

በዚህ ኢሰብአዊ ድርጊታቸዉ በዘር ማጠፋት ወንጀል እንደ ሂትለርና ግብረአበሮቹ መጠየቅና የኢትየያ ህዝብ ፍትህ ማግኘት ሲገባዉ ጭራሽ ወያኔ እነሱ የቀየሱትን የጥፋት እቅድ ወኪል በመሆን በኢትዮጵያ ስም የሚፈልጉትን እራሱ እየፈጸመላቸዉ ይገኛል።

## በህጋዊነት ሽፋን የተፈጸመ ወንጀል

ከአልጀርሱ ስምምነትጀምሮ በግልጽ እንደታየዉ የድንበር መካለሉ ዉጤት የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳና ህዝቡዋን የሚያዋረድ እንደሚሆን በብዙ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ አስቀድሞ የታወቀና የተጠበቀ ነበር። ለአለም ህዝብ ሰላምና ነጻነት ከፍተኛ ድርሻዋን ያበረከተችዉ ኢትዮጵያ በስሟ ስልጣን በያዙ የተደራጁ ሀይሎች ከፍተኛ ክህደት ተፈጽሞባታል። የሚከራከርላትና የራስዋን ግዛት የሚያስጠብቅላት መሪና መንግስት አጥታ ይሆታዋን እንድትለቅ ተደርጓል። ወያኔና ህሌና የሌላቸዉ አገልጋዮቹ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመቦርቦር ሆን ብለዉ የፈጸሙት ተግባር ራሳቸዉንም ከተጠያቂነት እንደማያድናቸዉ ዉጤቱም ለማንም እንደማይጠቅምና በአካባቢዉም ዘላቂ ሰላም መረጋጋትና እድገት እንደማያመጣ በደንብ አድርገዉ ሊያዉቁት ይገባል።

በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ስም የተፈጸመ ወንጀል

1. በታሪክም ሆነ በህግ የኢትዮጵያ አካል የሆነችዉ የአሰብና አካባቢዋ ጉዳይ እንዳይነሳ ወያኔ መሃል ሀገር ሆኖ በቋሚ ተጠሪነት ተከላክሏል።

2. በሰሜንና በሰሜን ምእራብ ያለዉን ድንበርም ሆነ ተብሎ በማለሳለስ የብዙ ሺህ ህዝብ ደም የፈሰሰበትንና የሀገሪቱዋ ሀብት የተሚጠጠበትን ይዞታችንን እንድናጣ ተደርጓል።


በዚህም ሳያበቃ ወያኔ አሰብን ማንም ሰዉ ማንሳት እንደሌለበት አስጠንቅቆ ስለድንበሩ የተወሰነዉንም ምንም ይሁን ምን እንቀበለዋለን በማለት አቋሙን በሚገባ አርጋግጦአል።እንደተለመደዉ ተንኮሉን ለመሸፈን ይህ የተደረገበትን ምክንያት ሲያብራራ «የህግን የበላይነት ሰላምና ዲሞክራሲን ለመጠበቅ ነዉ» በማለት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በድጋሚ ቀልዶአል።




ምእራባዊ ይዞታ

ምንጭ - www.ethiopiafirst.com

ይህ ከሆነ ታዲያ ከ100000 ሺህ ህዝብ በላይ እንዲሞትእንዲቆስልና እንዲሰደድ ለምን ተደረገ? ይህ ከሆነ ታዲያ ህዘባችን በርሀብ እየተጠበሰ ገንዘቡን እየተነጠቀ ለምን ለጦርነትና ለወያኔ ዝር ፊያ ተዳረገ?




ምስራቃዊ ይዞታ

ምንጭ - www.ethiopiafirst.com

የኢትራ ችግር ተቃለለ ወይስ ተወሳሰበ?

## ታሪክን ማጣመም ለምን?

ወያኔና ሻእቢያ የኤርትራን ጉዳይ በመንተራስ እዉት የኢትዮጵያን መሪዎች ማንነት (Image) ለማጥ ፋት ሙከራ አድርገዋል። በዚህ ጸረ-ታሪክ ኢላማዉ ዉስጥ የገቡት ለኢትዮጵያ ህዘብ ክብርን በማ ለብስ የመላዉ አለም ቅኝ ተገዢ ዝቦች የሚኮሩባቸዉን ያደዋዉ ጦር መሪንና ለድል ያበቁትን አጼ ምኒልክን ነዉ። በሁለቱ መካከል ልዩነት ቢኖር ሻእቢያ አጼ ዮሀንስ ምጽዋን ግዛቱ ነዉ ብለዉ አለ

መጠየቃቸዉንና እኤአ በ1884 ከእንግሊዞች ጋር ኢትዮጵያ እቃ በምጽዋ መኩል እንድታስገባ መስ ማማታቸዉን በመግለጼ ብቻ ነዉ።

ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ ያለዉን የከረረ ጥላቻ ለማየት ዛሬ እያየንና እየሰማን የሚገድላቸዉን አስሮ የሚያማቅቃቸዉንና የሚያሳድዳቸዉን ብቻ ሳይሆን በታሪክ ወደሁላ በመመለስ ለኢትዮያ በጎ የሰሩት ን ስማቸዉን ለማጉደፍ እንደሚጥር መገንዘቡ ትልቅ ብልህነት ነዉ። ምኒልክ ከተረከቡት ግዛት ዉስ ጥ ከማስፋት በስተቀር አሳለፈዉ የሰጡት ቦታ የለም። እዉነቱ ግን የኤርትራ አበዛኛዉ ቦታ በዚያ ዉ ባከባቢዉ ባላባቶች መሸጡ ነዉ። ለዚህ ማስረጃ «አጤ ምኒልክ» በሚባለዉ የፓዉሎስ ኞኞ መ ጽሃፍ ገጽ 139 ዉስጥ እንዲህ የሚል ተጽፎ ይገኛል።

> «አጼ ዮሃንስ ሲሞቱ እራስ መንገሻ ስልጣኑን እንዲወርሱ በመናዘዛቸዉ ዙፋኑ ለራስ መንገ ሻ አይገባም የሚሉት የመንገሻ ተቀናቃኝ የሆኑት የትግሬና የሃማሴን መኳንንት መንገሻን ለ መጉዳት በማለት ወደ ኢጣሊያ ገቡ። ታማኝነታቸዉን ለመግለጽም የመሬት ገጸበረከት አቀ ረቡ። ደጃዝማች ደብብ አስመራንና አካባቢዋን ደጃዝማች ባህታ ሀጎስ አካላ ጉዛይን ባላንባ ራስ ክፍለ የሱስ ክረንንና ቦጎስን ለኢጣሊያ መንግስት አስረከበዉ እነሱ ከኢጣሊያ መንግስ ት ስር ተገዢ ሆኑ።» በማለት በግልጽ አስቀምጦታል።

ከዚህም በተጨማሪ ከታች የተዘረዘሩትን አመታት ማየት ያለ ተጨማሪ ማብራሪያ በቂ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል።

- አሰብ በጣሊያኖች እጂ የገባቸዉ እኤአ 1869 ነዉ። በመቀጠልም እኤአ በ1882 ጣልየአኖች ከሉበት እስከ 40 ኪ.ሜ በማለፍ በታጣቂ ወታደር ከተቆጣጠሩት በሁ ዋላ በይፋ ቅኝ ግዛታቸዉ አድርገዉ አወጁ።
- ምጽዋን ደግሞ ከቱርኮች በሁዋላ እኤአ ከ1866-1885 በግብጾች እጂ ነበረች
- እኤአ በ1882 የነበሩት ንጉስ ደግሞ አጤ ዮሃንስ ነበሩ። እሳቸዉም እኤአ በ1884 የኢትጵያን እቃ በምጽዋ በኩል ለማሳለፍ ከእንግሊዞች ጋር ተስማምተዋል።ምጽዋ ንም የይገባኛል ጥያቄ አንስተዉ ማስመለስ አልቻሉም።
- አጤ ምኒልክ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩት ከ1889 ጀምሮ ነዉ።

እንግዲህ ላንባቢ ነገሩ ግልጽ የሆነ መሰለኝ! ታዲያ ለምንድነዉ ወያኔ ኤርትራን ምኒልክ አሳለፈዉ እንደሰጡ አድርጎ የሚያቀርበዉ? ለወያኔ ኤርትራ ማለት የትኛዉ አካባቢ ይሆን? ታሪክ በታሪክነቱ ሳ ይሆን በማንነት ላይ ተመረኩዘዉ መጻፋቸዉ ይሆን?

የ1889 የዉጨሌ ስመምነትም ቢሆን በጣሊያን ቋንቋ የተጭበረበረ ከመሆኑ በስተቀር የኢትዮጵያን ጥቅም ካለዉ ሁኔታ ጋር ሲታይ በትክክል የሚያስጠብቅ ነበር። መዘንጋት የሌለበት ነገር ኢትዮጵያ ስምምነቱን የፈጸመችዉ አለም በሙሉ በቅኝ ገዢዎች እጂ ወድቃ ሀገራችን ብቸኛ ነጻ ሀገር በነበረ ችበት ሰአት ከመሆኑም በላይ ጠላት በወታደራዊ በኢኮኖሚና በተክኖሎጂ እጂግ ከፍተኛ ብልጫ ባ ሳየበት ወቅት ነዉ።

ምኒልክ አርቲክል xvii
ተጭበረበረ መሆኑን ካዎቁ በሁላ የኢትዮጵያን ክብር ያስጠበቀ ፈጣንና አኩሪ እርምጃ በመዉሰድ በ አድዋዉ ታሪካዊ ጦርነትና ባስመዘገበነዉ ድል ማንኛዉንም ስምመነት ዉድቅ አድርገዉታል።

## የወያኔ መፍረክረክ

ወያኔ ከተጠነሰሰበት ጊዜ ጀምሮ አሁንም ወደ መጥፊያዉ በተቃረበበት ወቅት አብረዉት የሚጓዙት ከድተዉታል ወይም ተቃዉመዉት ራሱ አጥፍቶአቸዋል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከወያኔ ጋር አብ ረዉ የሰሩ ነገሩ እየገባቸዉ ሲመጣና አእምሯቸዉ እማይታዘዝበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ይታሰራሉ ወ ይም ይኮበልላሉ። ለምሳሌም ያህል አቶ ታምራት ላይኔን እነ አቶ ስየ አብርሃን አለማዝ ሚኮንና ሌ ሎችንም እጂግ ብዙ አገልጋዮቹን መጥቀስ ይቻላል።

እኤአ በማርች ወር 201 አ/ም አፈንጋጭ በመባል ከወያኔ አባልነታቸዉ የተባረሩት በከፍተኛ የስል ጣን መባለግና ገንዘብ በመዝረፍ ተወንጅለዋል። ይሁን እንጂ ዝርፊያዉንና በስልጣን መባለጉን የተያ ያዙት ገና ስልጣን ላይ እንደተፈናጠጡ ነበር። ይህም የኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ የተቃወመዉና ነጻ

ጋዜጦችም በየገጾቻቸው ላይ ከማስረጃዎች ጋር ይፋ ያደረጉት ጉዳይ ቢሆንም «ይህን የሚያወሩት ደርግ-ኢሰፓና ትምክህተኞች ናቸው በማለት» ወያኔ በማላገጥ አልፎት ነበር።

አፈንጋጭ በመባል የተባረሩት አባላት በበኩላቸው «እኛ ከሌላው ወያኔ የተለየነው ለሀገራችን ስለም ንቅረቀርና ለልዋእላዊነታችን ስንል ነው ብለዋል።» ለዚህም እንደማስረጃ የሚያቀረቡት አቶ መለስ የኢትዮጵያ ጦር ገፍቶ አዲቀይህና ሰነአፌ መከከል ሲደርስ ጦሩ ወደፊት እንዳይሄድ ትእዛዝ በመስጠት ክፈተኛ ክህደት ፈጽመዋል ብለዋል። ከዚያም በላይ አቶ መለስ ሆን ብለው አንድ ቢሊዮን ብር ኤርትራውያን ኢትዮጵያን እንዲዘርፉ ማድረጋቸውንና እራሳቸውም በቤተመንግስት በጀት እየተዳደሩ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ የማይወራረድ ልዩ በጀት እንዲተከልላቸው አድረገው ላለፉት አስር አመታት ይፋ ያልሆነ ሁለት ሚሊዮን ብር በያመቱ ማጋበሳቸውን አቶ ስዬና አቶ ታምራት ባቀረቡት ክስ ላይ አጋልጠዋል። ሁሉም ልክ ናቸው። ችግሩ የጸባቸው መንስኤ ለሀገርና ለወገን በመቆርቆርላይ የተመሰረተ አልነበረም።

የከረረ ጸብ ላይ የሚገኙት ሁለቱ ጎራዎች ማንኛቸውም ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ህዝብ አስበው ሳይሆን አንደኛው የሌላውን ጥቅምና ደህንነት በመጋፋቱና አደጋ ላይ በመውደቃቸው ለግል ጥቅምና አመለከከታቸው የሚያደርጉት የሞት የሽረት ትግል ነው።

ነገሩ የገባው የኢትዮጵያ ህዝብም ለምን ለኢትጵያ የቆሙ ከሆነ ፕሮፌሰር አስራት አስፋ ማሩ ዶ/ታየ ወ/ሰማያትና ሌሎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮያውያን ሲገደሉ በእስር ሲማቅቁና የሀገሪቱዋ ማንነት ክብሩዋና ሰንደቅ አላማዋ ጭምር ሲዋረድ ምንም አይነት ተቃውሞ አላሳዩ? በማለት መታዘብ ብቻ ሳይሆን ለነዚህ ሰዎች ሀገር ፍቅርና ልዋእላዊነት ምን ማለት ነው? በማለት እራሱን በመጠየቅአ አለፋቸው።

## ሰብአዊ መብት

እኢአ ከአፕሪል 11-18 በተማሪዎች ግምባር ቀደምነት በተካሄደው ህዝባዊ አመጽ ከ41 ሰው በላይ ሞቶ ከ500 በላይ ቆስሏል።

የቢ.ቢ.ሲ. ዜና ማሰራጫ በ05/30/01 *የኢትዮጵያ የ10 አመት ጉዞ ከመንግስቱ በሁዋላ* በሚለው ሰፊ ሃተታው ውስጥ በግልጽ እንዳስቀመጠው የኢፕሪሉ አመጽ የኢትዮጵያ ህዝብ ከወያኔ ጋር ያለውን ቅራኔ የሚያመለክት መሆኑን ከገለጸ በሁዋላ ኢትዮጵያ አሁንም ከአለም ውስጥ ካሉ የመጨረሻ ድሀ ሀገሮች አንዱዋ መሆኑዋን በፎቶገራፍ የተደገፈ ማስረጃ አቅርቦአል። ባለፉት አመታት የተለያዩ ዜና ማሰራጫወች እንደገለጹት የተራበው የህዝብ ቁጥር ከማንኛውም ጊዜ በልጦ እንጂ አንሶ አልተገኘም ።ይህም ወያኔ ያለፉትን መንግስታት ከመኮነንና ሀገሪቱዋን የባሰ ድህነት ውስጥ ከማስገባት በስተቀር አንዳችም የፈየደው ነገር እንደሌለ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ወያኔ ፕሮፌሰር አስራት ወ/የስን እ.ኢ.አ ከሀምሌ ከሃምሌ ወር 1985 አም ጀምሮ በእስር እንዲማቅቁ ካደረገ በሁዋላ ከሞት አፋፍ ላይ ሲደርሱ ክሳቸው እንኳን ሳይነሳ እ.ኢ.አ ታህሳስ 18 ቀን 1991 ለህክመና እንዲወጡ አደረገ። ሆኖም ግን በእስር ቤት ስለተነገላቱ ሀመማቸው ጸንቶባቸው ስለነበር እ.ኢ.አ ግንቦት 6 ቀን 1991 አ/ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል።

አቶ መኮንን ዶሪ አቶ አበራ የማነ አብና ሌሎችም እጂግ በርካታ የሆኑ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች እስካሁን ድረስ ታስረው በመማቀቅ ላይ ይገኛሉ። የግል ጋዜጠኞችን በማሰር በማስፈራራትና በማሳደድ ጸረ-ዲሞክራሲ መሆናቸውንም አስመስክረዋል።

ሌላው የወያኔ የጥፋት ኢላማ የሆነው ያኢትጵዮያ መምህራን ማህበር ነው። በማህበሩና በመምህራን ላይ ከፍተኛ ግፍ ተፈጽሟል። ይህንን ሃላፊነት የጎደለው የወያኔ ተግባር Steve Sinnott የተባሉት Ethiopia Teachers Education and Human Rights በሚለው ሪፖርታቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል " Teachers who had spoken out against the government's educational policies were dismissed from their posts. Dr. Taye W/semayat the association's president was imprisoned and held in appalling conditions. Ato Assefa Maru the Deputy General Secretary of the ETA, was assassinated by the government security forces, and the ETA General Secretary Ato Gemoraw Kassa was forced into exile in the UK."

# <u>አለም አቀፍ አሸባሪወችና ኢትዮጵያ</u>

እኤአ ሴፕተምበር 11 በኒውዮርክ የአለም አቀፍ ንግድ ማእከል ላይ አሸባሪዎች አደጋ ጥለው ብዙ ህዝብና ንብረት ማውደማቸው የሚታወስ ነው። ይህንን ሀላፊነት የጎደለው እርምጃ መላው ሰላም ወዳድ ህዝብና ለኢትዮጵያ ህዝብ የቆሙ ወያኔን የሚቃወሙ ድርጂቶች አውግዘውታል።

ወያኔም እንደተለመደው የተፈጠረውን ቀውስ ለመጠቀም የራሱን አሸባሪነት ለመደበቅ ሲል ድረጊቱ ባስቆጣቸው ሀገሮች ፊት ጸረ-አሸባሪ ሆኖ ለመታየት ጩሀቱን ከፍ አድረጎ ማስመሰል ጀምሮአል።ይሁን እንጂ የወያኔን አሸባሪነትና ከአሸባሪዎች ጋር መስራት የኢትዮጵያ ህዝብ ባቻ ሳይሆን ከላይ የጠቀስናቸው ሀገሮችም ቢሆኑ ሊጠፉቸው አይቸልም። ወያኔን በታችና ዘረኛ በሆነው ጸረ-ህዝብ ፕሮፓጋንዳ በመታገዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸመው የማሳደድና የጭፍጨፋ ተገባር ሊውል ሊያድረ ይችላል አንጂ ከቶውንም ባሸባሪነት ከመጠየቅ ሊያድነው አይችልም።

ትናንት ከሻእቢያ ከኦጋዴን ነጻ አውጭና አክራሪዎች ጋር ሆኖ በኢትዮያ ህዘብላይ ሸብር ሲያካሂድ የነበረ ድርጂት ዛሬ ሱማሊያ ዉስጥ አሸባሪነትን እየተዋጋሁ ነው ማለቱ ስልጣን ላይ ለመቆት ነው እንጂ ምንም ለሃገር የመቆርቆረና ኢትዮጵያዊነት ባህርይ እንደሌለው በራሱ በኖቤምበር 1980 በሶማሊ ትግራይና ኦሮሞ Resistant movement ለንደን ውስጥ 'STORM' በሚባል ኒውስለተራቸው በጋራ ያሰራጩትን ከዚህ በታች ያለውን ጽሁፍ መመልከቱ በቂ ማስረጃ ነው።

> "The colonisation of the Somalis by the Amharas feudal armies began with the conquest of Harar. This struggle of the Somali under Ethiopian rule is generally presented to the world by the mass media as a 'border dispute' between Ethiopia and Somalia. <u>It is nothing of the kind.</u>
>
> The Western Somali (Ogaden) People, just like the Eritreans, Oromos the Namibians Palestinians and the Saharawis are fighting against an oppressive colonial rule."

በዚህ ኒውስ ሊትር ውስጥ አማራን በመጥላትና ለማስጠላት ለጻፉት አርካሽ ጸረ-ኢትዮጵያ የውሸት ፕሮፓጋንዳ መልስ መስጠቱ ከጽሁፋቸው ተራነት የተነሳ የኢትዮጵያን ህዝብ ክብር ስለሚነካ ትተነዋል። ጽሁፉን አግኝቶ ማንበቡ (ከዚህ ጽሁፍ መጨረሻ ዋቢ መጻህፈትን ይመልከቱ) ግን ስለ ወያኔም ሆነ ስለ ሌሎች ጸረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ትልቅ እውቀት ያስገኛል። እንግዲህ የወያኔ ሽብረተኝነትን እየተዋጋሁ ነው ማለትን ለኢትዮጵያና ለመላው አለም ሰላም ወዳድ ህዝብ ትተነዋል።

## <u>ማጠቃላያ</u>

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንደተመለከትነው ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ከፍተኛ ችግር ላይ ትገኛለች። ስለሆነም በኢትዮጵያዊነትና በጸረ-ኢትዮጵያዊነት መካከል የከረረ ትግል በመካሄድ ላይ ነው።

<u>የወያኔ ጸረ-ህዝብ እንቅ</u>ስቃሴ የተመሰረተው በዲሞክራሲና በብሄረሰብ ስም ስለሆነ ድርጂቶችም ሆኑ ግለሰቦች ሴራውን በትክክል በመገንዘብ ማጋለጥና ሙሉ በሙሉ ከህዝብ እንዲለይ ማድረግ ያስፈልጋል።

ጠላት ጥቃት ማካሄድ የጀመረው ለኢትዮጵያ በጎ በሚያስቡና ባጠቃላይ በጥቅምና ደህንነታችን ላይ ብቻ ሳይሆን <u>የአንድነታችንን እድገት</u> በሚያሳየው ታሪካችን ላይ ጭምር መሆኑን በመረዳት ታሪካችን በሚገባ ማጥናትና ማንነታችንን መረዳት።

<u>የተለያዩ አቅጣጫ ይዘው ወያኔን የሚታገሉ የህብረ-ብሄርም ሆኑ የብሄረሰብ ድረጂቶች በመሰረታዊ አላማቸው ላይ በመመርኮዝ ለህዝባቸው ጥቅምና ደህንነት ሲሉ በጋራ ጉዳዮች ላይ አብረው እንዲሰሩ ማበረታታትና ድጋፍ መስጠት።</u>

አሉባልታና ጥላቻ ነኸ የጥፋት መልእክተኞችን መለየትና መስመራቸውን ማጋለጥ። ህዝቦችን አዘናጊና ጥቃትን ለዩነቶችን ወደጎን በመተው የጋራ ጠላትን ለመመከት ብሎም ድል በመምመታት እውነተኛውን ዲሞክራሲ በማስፈን የብሄርብሄረሰቦችም ሆነ የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ደህንነትና ጥቅም እንዲጠበቅ ማድረግ።

ወያኔ በዲሞክራሲ ስም በዉጭ ሃይሎች የሚታገዝ ስለሆ ጸረ-ዲሞክራሲ ጸረ-አነድነትና ጸረ-እድገት መሆኑን በዉጭም ሆነ በሀገር ዉስጥ ላሉ ሰላምና ፍትህ ወዳድ ህዘቦች በተኘዉ አጋጣሚ ሁሉ ማስ ርዳት።

*ዋቢ/መረጃ መጸሀፍት*


Bahiru Zewude. (1991) A History of Modern Ethiopia 1855-1974 – (Eastern African Studies).

Chris Prouty and Eugene Rosenfeld (1982). Historical Dictionaries of Ethiopia. African Historical Dictionaries no. 2.

ሜጀር ጀኔራል ነጋ ተገኝ (እአ.አ 1993) የኢትዮጵያዉያን የረጂም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ስራዊ ት አመሰራረት 1855-1974። ጣና ማተሚያ ቤት ቶሮንቶ ካናዳ።

ዮሀንስ መመሸሻ (1996) ኢትዮጵያ አስተዳደርና ፖለቲካዊ ሂደት። ሎስአንጀለስ።

Ethiopian Register (Feb.1999.) Vol.6, no. 2. Avon,USA.

ጳዉሎስ ኞኞ (እአ.አ 1984) ዳግማዊ አጤ ምኒልክ።የመጀመሪያዉ መጽሀፍ።

Sinnott S. (Dec.2000). Ethiopia Teachers Education and Human Rights. A Report of Education International Mission to Ethiopia.

http://www.ethiopiafirst.com/